ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ ሐተታ
ነሐሴ 4 ቀን 2010 ዓም

# የአመኑት ፈረስ ፤ ጣለ በደንደስ

ኢትዮጵያን ለመምራት ፤ ራዕይና በቂ ዝግጅት አለኝ ብሎ በራሱ የሚተማምን ድርጅት ፤ መነሻውና መድረሻው የመላውን ሕዝቡ ያልተቆጠበ ድጋፍ አግኝቶ መንቀሳቀስ እንደሚኖርበት ሊዘነጋው አይገባም። ይኽ ሁኔታ ግን በቅርቡ የሀገሪቱ ታሪክ አልተከሰተም። የሚፈራረቁት አገዛዞች፤ የመላውን ሕዝብ ፍላጎትና ተስፋ ያነገቡ ሳይሆን፤ በተቃራኒው፤ የጥቂት ግለሰቦችንና የወገኖቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርአት እየመሠረቱ ቆይተዋል። አሮጌው አምባገነን አገዛዝ በአዲስ አገዛዝ እየተተካ ፤ የሕዝቡን ግፍና በደል ወደባሰ አዘቅት የሚጥል እንጅ ፤ የተሻለ ሁኔታን የሚያመጣ አልነበረም። ሕዝቡ ግን ለተሻለ አስተዳደርና ለዴሞራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚያደርገውን ትግል አቋርጦ አያውቅም። እንዲያውም ፤ በየጊዜው ውድ ዋጋ የሚጠይቀውን የሕይወት መሥዋዕት እየከፈለ ዐመፁን ከመቀጠል አልቦዘነም። ከፍተኛ መሥዋዕት ያስከፈለው ትግል ግን እስካሁን ድረስ የተጠበቀውን ሕዝባዊ ድል አላስመዘገበም። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስካሁን በኢትዮጵያ አልተመሰረተም ።

ለአለፉት ግማሽ ምዕተ ዐመት፤ በሕዝብ ዐመፅ ሦስት ታላላቅ ለውጦች መፈራረቃቸው ቢመዘገብም ፤ የሕዝቡ የለውጥ ዕድል ግን ፤ ሦስት ጊዜ ጠበንጃ ባነገቱ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ተነጥቋል። የሕዝቡም ትግል የተፈለገውን ውጤት ሳያስገኝ ቀርቷል። የመጡት ለውጦች ፤ በሕዝብ ትግል መሥዋዕት መሆኑ ማንም ሊክደው አይችልም። የሕዝቡ ትግል ያስገኘውን ለውጥ፤ ማንም ኃይል ወይም ድርጅት አልመራውም። የታሪክ ዕውነታን ባግባቡ መስቀመጥ ካስፈለገ፤ የሕዝቡ ትግል ያስገኛቸውን ለውጦች በግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ፤ ያሁኑ ሕዝባዊ ለውጥ ፤ መነሻው ከየት ነው ? ሂደቱና አቅጣጫው ወዴት እያመራ ይገኛል ? መዳረሻውና መቋጫው ምን ሊሆን ይችላል? የሚሉትን ጥያቄዎች መመርመር ፤ የወደፊቱን ጮራ ፍንጣቂ ለማየት ያስችላል። ዛሬ የተከሰተው የለውጥ ወላፈን ፤ የዜጎቹን ቀልብ መሳቡ ባያከራክርም፤ የቀልብ ስበቱ ካስገኘው ፈንጠዝያ ባሻገር ሊመጣ የሚችለውን ተጨባጭ ኹነት በቅጡ የመረዳት አስፈለጊነቱ ግን አያጠያይቅም።

የታሪኩ ባለቤት እራሱ ሕዝብ ስለሆነ፤ ካለፉት አምሳ ዐመታት ወዲኽ መሥዋዕት ከፍሎ ያስመዘገባቸውን ለውጦች ሁሉ፤ እንዴት እንደተነጠቀ ተገንዝቧል። የሚያስገኛቸውን እንደገና ሳይነጠቅ የለውጡን ፍሬዎች ለመብላት፤ አሁንም የዐመፅ ትግሉን ቀጥሏል ።

1ኛ. የ1966 ዓም ዐብዮታዊ አመፅ ያስገኘውን ሕዝባዊ ድል ፤ ደም በተጠሙና የሥልጣን ሱስ ባሰከራቸው ጥቂት ወታደራዊ መኮንኖች ተነጠቀ። ለአስራ ሰባት ዐመታት ፤ የመከራና ፍዳ ዘመን አሳለፈ። ሀገሪቱም በደም አላባ ተጥለቀለቀች። እናት መካን ሆነች። ሀገር ብርቅየ ልጆቿን አጣች። በደርግ ካድሬዎች ፤ ያንድ እናት ልጆች ፤ እርስ በእራሳቸው እንዲተላለቁ ተደረገ። የሀገራችንም አኩሪ ታሪክ ባሳፋሪ ድባብ ተጠናቀቀ ።

ቀን ሲጨልም ፤ ሰማይ ምድሩ መደፋቱ አይቀርምና ፤ ደርግን ሲደግፉ የነበሩ መንግሥታትና ሌሎች ባዕዳን ኃይሎች ፤ በጠራራ ፀሀይ ያን ጨቋኝን ሥርዓት አጋልጠው ከዱት። "ያመኑት ፈረስ፤ ጣለ በደንደስ" ሆነና፤ የሕዝቡን የትግል ዐመፅ ማንም ኃይል የሚያቆመው አለመኖሩን ተገንዝበው፤ ደርግን አባርረው፤ በርሱ ምትክ፤ አዲስ አገልጋይ ፈጥረው ፤ ወያኔ የሚባል ከሃዲ ቡድን በቦታ አስቀመጡ። ያስራ ሰባት ዐመታት ሕዝባዊው ዐመፅም ተጨናገፈ። ኢትዮጵያና ዜጎቿ ተከዱ። ደርጎችም በሚያሳፍር ታሪክ ሕዝቡንና ሀገሪቱን ከድተው ሸሹ። ይኽ ደግሞ፤ አሳፋሪ የታሪክ ጠባሳ ትቶልን አልፏል። ኢትዮጵያ ሀገራችን ፤ የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የዕሩቅ ዘመድ አጥታለች። በአውላላ ሜዳ ላይ ወድቃ፤ አይዞሽ የሚላት አጥታ ቀረች ! ሕዝቦቿም ተባብረው ሊቆሙላት አልቻሉም ።

2ኛ. የ1981 ዓም የተገኘውን ልውጥ ያመጣው ያስራ ሰባት ዐመት መራራ ሕዝባዊ ትግል ወጤት ነበር። ሁኔታውን በአግባቡ መጠቀም የሚችል የተዳራጀው ኢትዮጵያዊ ኃይል በሎንዶኑ ስብሰባ እንዳይገኝ ተከልክሎ ፤ ነፍጥ አንግበው በብሄር የተሰባሰቡ ፀረ- ኢትዮጵያ ኃይሎች ብቻ ፤ በባዕድ ኃይል ታግዘውና ተመርተው አምባገነናዊ አገዛዝ ለመመስረት የሚያስችላቸው ስብሰባ ብቻቸውን እንዲሳተፉ ተደረገ። ይኽ ሊሆን የቻለው ፤ በስመ-ጥፉው የሎንዶን ስብሰባ ነበር። የዚሕ መርዘኛ ስብሰባ አቀነባባሪ ኽርማን ኮሆን የተሰኘ የአሜሪካ ባለሥልጣን ነበር። ይኽ ግለሰብ ፤ በጉባዔ ላይ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም ማስጠበቅ የሚችሉ ኢትዮጵያውያን ኃይሎችን አስከልክሎ ፤ የራሱን ሀገር ጥቅም ሊያስጠብቁ ይችላሉ ያላቸውን ፤ ታማኝ አጋልጋዮቹን ወያኔዎች ፤ በስብሰባ እንዲካፈሉ አስደረገ። ይኽንን ወንጀል በመፈፀሙ፤ የቱን ያኽል የሀገራችን ኢትዮጵያ መርዘኛ ጠላት መሆኑን በተግባር አስመሰከረ። ከዛሬው ይመሳሰላል፡፡

በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመውን ታሪካዊ ወንጀል ለመሸፋፈን ይመቸኝ ይሆናል ብሎ በማሰብ፤ አንድ የዲፕሎማሲ ቅላፂ፤ በምፀት ተናገረ። ይኸውም፤ "ወያኔ ዴሞክራሲን ካላመጣ እርዳታ አያገኝም" አለ። ጥቂት ተላላዎችን ሊያደናግር የቻለ ቢሆንም ፤ መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ግን ሊያወናብድ ዐቅም አልነበረውም። ይኽ ዘረኛ አገዛዝ፤ የመሰረተው ዴሞክራሲ ሥርዓትን ሳይሆን፤ አምባገነንነትንና የሀገሪቱን ዜጎች በዘርና በጎሣ መከፋፈልንና ፤ ሃብት ንብረት መዝረፍን ነበር።

በጋሻ-ጃግሬነት የሚያገለግላቸው ባዕዳንም፤ ይህንን ግፍና በደል ፤ እያዩ እንዳላዩ ሆነው ተባበሩት እንጅ፤ አልነቀፉትም። እንዳያውም አልፈው -ተርፈው ያልተቆጠበ፤ የገንዘብ፤ የጦር መሳሪያ፤ የቁሳቁስ፤ የመረጃና የዲፕሎማቲክ እርዳታ ሲያጎርፉለት ቆይተዋል ። **ከዚህ በቀር፤ እጅግ የሚያስቆጨውና እንደ ዕግር ዕሳት የሚያንገበግበው በደል፤ ለሃገሩ አንድነትና ነፃነት ፤ በየበረሃውና ጠረፉ ሲንገላታ የኖረውን መከላከያ ሠራዊት በአንድ ቀን ጀምበር ተበታትኖ እንዲፈርስ መደረጉ ነበር። ያ ሠራዊት፤ ያላንዳች ክብርና ምስጋና ሜዳ ላይ ወድቆ፤ የዕለት ጉርሱን ለማግኘት በጎዳና ላይ ምጽዋት ሲለምን ማየት ልብ ይሰብራል።**

**3ኛ.** አሁን በመካሄድ ላይ ያለውን ለውጥ ያመጣው የሕዝብ ዐመፅ ነው። የሃያ ሰባት ዐመታት መራራ የሕዝብ ትግል ወጤት ያስገኘውን የለውጥ እንቅስቃሴ በአግባቡ መከታተልና በየፈርጁ እየገመገሙ ሲሆን የሚገባውን ማድረግ ወሳኝነት አለው። ይኽ ህዝባዊ ዐመፅ እያሳየ ያለው ለውጥ የሕዝቡ የትግል ውጤት በመሆኑ፤ ባለቤቱም እራሱ ሕዝቡ መሆኑ አያከራክርም። ከባድ መሥዋዕትን ያስከፈለ ትግል ውጤት በመሆኑም ፤ የለውጥ አጋጆች እንዳይነጥቁት መከላከል፤ የለውጥ ፈለጊው ተግባርና ኃላፊነት ነው።

ግላሰቦችን ብቻ ማዕከል አድርጎ መንቀሳቀስ፤ ለለውጡ ሂደትም ሆነ መዳረሻ ፤ ዋስትናን አይሰጥም። ይኽም በታሪካችን የታየ እነደሆነ አይዘነጋም። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ከእንግዲኽ ወዲያ ማመን የሚገባው ፤ እርሱ ራሱ በሚመሰረተውና በሚቆጣጠረው **ተቋም** እንጅ ፤ በግለ ሰቦችና በስብስቦች መሆን አይገባውም።

የአሁኑን ለውጥ እንቅስቃሴ አካሄድና ፍጥነት በሁለት ዐተያየቶች የሚፈርጁት ወገኖች እንዳሉ ይስተዋላል። ይደመጣል። በአንድ ወገን ያሉት፤ ለውጡ አዝጋሚና ዳተኛ በመሆኑ፤ ለስር ነቀል ለውጥ ምልክት ፍንጭ አላያሳየም የሚሉ ሲሆን፤ ሌላኛዎቹ ደግሞ እጅግ ፈጣን እየሆነ በሜድ ላይ ስለሆነ ከአንድ ግለሰብ ቁጥጥር ውጭ እየሆነ መምጣቱ ስላማይቀር ፤ አዳናቃፊዎቹ ፤ ለውጡን በአፍ-ጢሙ ለመድፋት መሞከራቸው ስለማይቀር ፤ የለውጥ ተጻራሪዎች ሁሉ፤ አመች ሁኔታን ሊፈጥርላቸው ይችላል የሚል ነው። ይኽንንም ሰበብ በማድረግ፤ ሁከትና ብጥብጥ አነሳስተው፤ የራሳቸውን አጀንዳ ለማስፈፀሚያ ሊጠቀሙበት ይችላሉ የሚል ስጋት አይኖርም አይባልም። በሌላ በኩል ሲታይ፤ የነኝኽ ስጋቶች ምንጭ ፤ የለውጡን እንቅስቃሴ የሚመራ ጠንካራ ተቋም ያለመኖሩ ምክንያት እነደሆነ መገንዘብ አያዳግትም ። ማነኛውም ሀገር ፤ ተቋማትን መስርቶ ካልተንቀሳቀሰ ፤ ጥረቱ ሁሉ የዕምቧይ ካብ ሆኖ እንደሚቀር የሀገራችን ሁኔታዎች በተደጋጋሚ የሚያስረዱት ሀቅ ነው። ለውጡን የሚመራ አስተማማኝ ተቋም መኖር አለበት የሚሉ ቁጥራቸው እየበረከተ መጥቷል። ሁሉን ዐቀፍ የሽግግር ሂደት ይጀመር፤ የሽግግር መንግሥትም ይቋቋም የሚለው የሕዝብ ጩኽት ያለምክንያት አይደለም ።

የዚኽ ለውጥ እንቅስቃሴ ያሰደነገጠው ወያኔን መሆኑን ማየት ይቻላል። በዚኽም ተባለ በዚያ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የለውጥ እንቅስቃሴ እየተጠናከረ መሄዱ ታሪካዊ ሃቅ በመሆኑ፤ አስተዋዩ የትግራይ ሕዝብ የለውጡ ሙሉ ተባብሪ ሆኖ እንደሚዘልቅ ተፈጥሯዊ ነው ።

ይኽ ግንዛቤ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ እንቅስቃሴውን በሁለት ተፃራሪ ጽንፎች ድባብ አስገብቶ ከመፈረጅ ይልቅ፤ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እየገመገሙ መከታተልና ተንገራግጮ እንዳይቀር አስፈላጊውን መከላከልና እንክብካቤ መደረግ አለበት የሚሉ ወገኖች ቁጥር ቀላል አይደለም። ይኽ ህዝባዊ አመለካከት ፤ እውነትነት ያለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ ሌላ አማራጭ እንደሌለውም ይገመታል።

የለውጡ እንቅስቃሴ ካስገኛቸው ትሩፋት፤ የእስረኞቹ መፈታት እንደሆነ ብዙዎቹ የሚስማሙበት መሆኑ ባይካድም፤ ለአያሌ ዐመታት በወህኒ ቤት የሚሰቃዩና ፤ መዳራሻቸው የት እንደሆነ የማይታወቁ የኢሕአፓ አባላትና ሌሎችም እስካሁን ድረስ

በዘግናኝ  ሁኔታ ላይ ናቸው። እስካሁን እነርሱን ለመፍታት የደፈረ አልተገኘም። ድርጅታቸውና ቤተሰቦቻቸው  አሁንም ህጋዊ ጥያቄዎቻቸውን አንግበው  በጉጉት ይጠባበቃሉ።  ፓርቲው የአባላቱንና የሁሉንም  መፈታት ጥያቄ በዋናነት አንግቦ ይታገላል።  የታሰሩበት አባላት ነፃነት  ከኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ መውጣት አለመውጣት ጋር የተያያዘ በመሆኑ፤  የፓርቲው ቀዳሚይ የትግል ትኩረት በሃገራችን ነፃ መውጣት ላይ በመሆኑ፤ የለውጡ እንቅስቃሴ በአቸነፊነት እንዲጠናቀቅ  ከሕዝቡ ጎን ሆኖ ይታገላል።

የወያኔ ደጋፊዎችና ተባባሪዎች ፤  "**ያመኑት ፈረስ  ጣለ በደንደስ** " እንደሚባለው ፤ የሕዝቡ  ዐመፅ እያየለ ሲመጣ እንደሚከዱት የታሪክ ሀቅ ነው።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !